አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ መጋቢት ፯ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th year No. 10
Addis Ababa 16th day of March 2023

<u>ማውጫ</u>

**ደንብ ቁጥር ፲/፳፻፲፭**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት እና ህዝባዊ ድርጅት ተሿሚዎች እና ሠራተኞች የሥነ- ምግባር ደንብ**

**ገጽ------------------------------------ ፫፻፺፰**

<u>**CONTENTS**</u>

**Regulation No. 10/2015**

**Addis Ababa City Administration Public Office, Public Enterprises and Public Organization Appointees and Employees Code of Conduct**

**Page ------------------------------------------------398**

<u>**ደንብ ቁጥር ፲/፳፻፲፭**</u>

<u>**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት እና ህዝባዊ ድርጅት ተሿሚዎች እና ሠራተኞች የሥነ- ምግባር ደንብ**</u>

ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ፣ በህዝብ አገልጋይነት መንፈስ የሚተጋ እና የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ተግባራዊ የሚያደርግ ትጉህ የተቋም ተሿሚና ሠራተኛ መፍጠር በማስፈለጉ፤

የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት እና ህዝባዊ ድርጅት አካላት ለህብረተሰቡ የሚያቀርቡት አገልግሎት ከብልሹ አሰራር የፀዳ እንዲሆን በማድረግ የእድገትና የዴሞክራሲ ግንባታ ተግባራት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ማድረግ በማስፈለጉ፤

<u>**Regulation No. 10/2023**</u>

<u>**Addis Ababa City Administration Public Office, Public Enterprises and Public Organization Appointees and Employees Code of Conduct**</u>

**WHEREAS,** it has been found necessary to create hardworking appointees and employees of institutions who are free from corruption and malpractices, strive in the spirit of public service and apply ethical principles;

**WHEREAS,** it is found necessary to ensure that the services provided by Public Offices, Public Enterprises and Public Organizations to the public are free from corruption so that development and democracy building activities continue to be strengthened;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፻፬፻፵፭
**Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445**

የሥነ-ምግባር ጥሰትና ብልሹ አሰራር ድርጊት ውስጥ የሚገቡ የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት እና ህዝባዊ ድርጅት ተሿሚዎች እና ሠራተኞች ተጠያቂ የሚሆኑበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፸፭/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት እና ህዝባዊ ድርጅት ተሿሚዎች እና ሠራተኞች የሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር ፲/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ምክር ቤት"** ማለት እንደአገባቡ የከተማ ፣ የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ ምክር ቤት ነው፤

፬. **"አዋጅ "**ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፸፭/፪ሺ፲፬ ነው፤

፭. **"የመንግሥት መሥሪያ ቤት"** ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በአስተዳደሩ በጀት የሚተዳደርና የከተማ አስተዳደሩ ሥራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መሥሪያ ቤት ነው፤

**WHEREAS,** it has been found necessary to establish a procedure system in which appointees and employees of Public Offices, Public Enterprises and public organizations who engage in ethical violations and malpractices are held accountable;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Sub Article (1) of Article 22 of the Addis Ababa City Administration Ethics and Anti-Corruption Commission establishment proclamation, the Addis Ababa City Council has issued this Regulation.

## Part one
## General Provisions

**1. Short title**

This Regulation may be cited as: "Addis Ababa City Administration Public Office, Public Enterprise and Public Organization Appointees and Employees Code of Ethics No. 10/2023".

**2. Definition**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the Addis Ababa city;
2. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Council"** means a city, sub-city or district council, as appropriate;
4. **"Proclamation"** means Addis Ababa City Administration Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation No. 75/2022;
5. **"Public Office"** means any office that is fully or partially run its activities by the budget of the city government and where the activities of the city administration are carried out;

፮. **"የመንግሥት የልማት ድርጅት"** ማለት የአስተዳደሩ የባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የአስተዳደሩ የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ማኅበር ነው፤

፯. **"ህዝባዊ ድርጅት"** ማለት በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከሕዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሀብትን የሚያስተዳድር አካልንና አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ሲሆን የሚከተሉትን አያካትትም፡-

ሀ) የሀይኖማት ድርጅት፣

ለ) የፖለቲካ ድርጅት ወይም ፓርቲን፣

ሐ) የዓለም አቀፍ ድርጅትን፣ እና

መ) ዕድርና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ማህበርን፤

፰.**"ኮሚሽን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው፤

፱. **"ተቋም"** ማለት ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ሲባል የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ነው፤

፲. **"የተቋሙ የበላይ ኃላፊ"** ማለት የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅትን ወይም ህዝባዊ ድርጅትን የሚመራ ዋና የስራ ኃላፊ ነው፤

፲፩.**"ሠራተኛ"** ማለት በአንድ ተቋም ውስጥ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሰራ ግለሰብ ነው፤

6. **"Public Enterprise"** means a public enterprise or share company where the city government has a full or partial ownership;

7. **"Public Organizations"** means an organ that manages money, property, or other resources that are collected in any way from members or the public or for providing public services, and includes the relevant companies from the private sector; however, it shall not include the following:

A. Religious institutions;

B. Political organizations or parties;

C. International organizations; and

D. *'Idir'* and other similar cultural and religious associations;

8. **"Commission"** means Addis Ababa City Administration Ethics and Anti-Corruption Commission;

9. **"Institution"** for purposes of this regulation means a Public Office, public Enterprise or public organization for the;

10. **"Head of the institution"** means the head of a Public Office, Public Enterprise or public organization;

11. **"Employee"** means an individual who is permanently or temporarily employed in an Institution.

፲፪. **“ተሿሚ”** ማለት በየደረጃው ያለ የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤት፣ በልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ በኃላፊነት እንዲያገለግል የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው ሲሆን የቦርድ አባልን ይጨምራል፤

፲፫. **“ጠቋሚ”** ማለት ሊፈጸም ነው ብሎ ያመነውን ወይም የተፈጸመ የሙስና ወንጀል ወይም የሀብት ምዝገባ ትክክለኛ አለመሆኑን የሚመለከት መረጃ ለኮሚሽኑ ወይም ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፬. **“ሥነ-ምግባር”** ማለት የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት ወይም ህዝባዊ ደርጅት ተሿሚዎች እና ሠራተኞች ስህተት የሆኑ ድርጊቶችን ወይም ተግባሮችን እንዳይፈፅሙ፣ ትክክል የሆኑትን ደግሞ በቀና አስተሳሰብ እንዲፈፅሙ የሚያስችል ድርጊት ነው፤

፲፭. **“ሚስጥራዊ መረጃ”** ማለት በህግ እንዳይገለጽ የተከለከለ መረጃ ነው፤

፲፮. **“የሥነ-ምግባር ጥሰት”** ማለት በዚህ ደንብ ውስጥ የተካተቱ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን የሚቃረን ማንኛውም ድርጊት ነው፤

፲፯. **“የሥነ-ምግባር መርሆዎች”** ማለት በመንግስት መሥሪያ ቤት ፣ በልማት ድርጅት ወይም ህዝባዊ ድርጅት መስሪያ ቤቶች ውስጥ መደረግ ያለባቸውና የሌለባቸው ድርጊቶች የሚገለፁባቸው አጠቃላይ የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት እና የተግባር አፈጻጸሞች የሚመሩበት ሥርዓት ነው፤

12. "**Appointee**" means a person who has been appointed or assigned to serve in a position in a city Public Office, Public Enterprise or public organization at any level and includes a board member;

13. "**Whistleblower**" means any person who submits information to the Commission or ethics monitoring units that he believes is about to be committed or has been committed.

14. "**Ethics**" means an action that allows appointees and employees of a Public Office, Public Enterprise or public office not to do wrong actions or actions, and to do the right ones with an honest mind;

15. "**Confidential Information**" means information prohibited from disclosure by law;

16. "**Violation of Ethics**" means any act that violates the ethical principles contained in this Regulation.

17. "**Principles of ethics**" means the general system of thought, attitude and performance that defines what should and should not be done in the offices of a Public Office, Public Enterprise or public organization;

፲፰."**የጥቅም ግጭት**" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከመንግስት ወይም ከሕዝብ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ወይም የሚቃረን ማንኛውም ጥቅም ነው፤

፲፱."**ሀብት**" ማለት ማንኛውም የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ንብረት ሲሆን የመሬት ይዞታንና ዕዳን ይጨምራል፤

፳."**ገቢ**" ማለት በመንግስት መሥሪያ ቤት፣ በልማት ድርጅት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ውስጥ ያለ ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ በመቀጠርና ከመንግስት የሥራ ሰዓት ውጭ በትርፍ ጊዜው የሚያገኘው ወይም ከአክሲዮን የሚገኝ ገቢ፣ በስጦታ ውርስ ወይም ቀጣይነት ያለው ከውጭ ሀገር የሚገኝ የቤተሰብ ድጎማ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፤

፳፩. "**ጥቆማ ማቅረብ**" ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት፣ በልማት ደርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ ያለ ማንኛውም ተሿሚ እና ሠራተኛ በሥራው አጋጣሚ የሚያያቸውን ብልሹ አሰራሮችና ተግባራትን ለሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ወይም ለኮሚሽኑ ጥቆማ ማቅረብ ነው፤

፳፪. "**ተገቢ ያልሆነ ባሕርይ**" ማለት ከዚህ የሥነ ምግባር ደንብ እንዲሁም ተቀባይነት ካለው የማህበረሰቡን ባሕላዊ አኗኗር የሚቃረን ማናቸውም ድርጊት ነው፤

፳፫."**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፬. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

18. "**Conflict of interest**" means any interest that directly or indirectly conflicts with government or public interest;

19. "**Property**" means any property immovable or movable or tangible or intangible and includes land and debt;

20. "**Income**" means earnings any appointee or employee in a Public Office, Public Enterprise or public organization earns during his spare time outside of government working hours, or income from shares, gift inheritance or continuous family rimitance from abroad and the like;

21. "**Suggestion**" means any appointee or employee in a Public Office, development agency or public organization to make a suggestion to the ethics monitoring unit or the Commission regarding corrupt practices and activities that they see in the course of their work;

22. "**Inappropriate behavior**" means any act that is contrary to this code of conduct and the accepted cultural way of life of the community;

23. "**Person**" means any natural or juridical person;

24. In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine.

**፫. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በከተማ አስተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅት ተሿሚዎች እና ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፬. የደንቡ ዓላማዎች**

ይህ ደንብ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅት ተሿሚዎች እና ሠራተኞች የሥነ-ምግባርና የሞራል እሴቶችን በመገንባት ለፀረ ሙስና ትግሉ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ፤

፪.ተሿሚዎች እና ሠራተኞች የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ተገንዝበውና የላቀ ሥነ-ምግባር ኖሯቸው ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል የተጣለባቸውን የመንግሥትና የህዝብ አደራና ኃላፊነት በብቃት እንዲወጡ ማስቻል፤

፫. ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንፃር በላቀ ሥነ-ምግባር በመመራትና በመከተል የጥቅም ግጭትን መከላከል፤

፬.የሥነ-ምግባር ግድፈቶችን እንዳይፈፀሙ ማስገንዘብ፣ ተፈፅመው ሲገኙ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የግልፅነት እና የተጠያቂነት አሰራር ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ እሴቶችን በመፍጠር ዜጎች በመንግስት ላይ አመኔታ እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡

**፭. ኃላፊነት**

ማንኛውም የተቋም የበላይ ኃላፊ ፡-

፩.ይህን የሥነ-ምግባር ደንብ በሚገባ አውቆ ሥራ ላይ ለማዋል ሠራተኞችን የማስተማርና የማሳወቅ፤

**Scope of application**

This Regulation shall be applicable to the appointees and employees of the city Administration Public Office, Public Enterprise and public organization.

3. **Objectives of the regulation**

This regulation shall have the following objectives:-

1. To build the moral and ethical values of appointees and employees of Public Offices, Public Enterprises and public organizations so that they can play their part in fight against corruption;
2. To make sure Appointees and employees are aware of the principles of ethics and have superior ethics to prevent corruption and malpractice, to enable them to effectively discharge their government and public duties and responsibilities;
3. To prevent conflicts of interest by leading and following superior ethics in terms of their responsibilities;
4. To remind people not to commit ethical lapses, to take corrective action when they are found, by creating values that help to implement a system of transparency and accountability, so that citizens have confidence in the government.

4. **Responsibility**

Any Head of Institution shall have responsibility of:-

1. Educating and informing employees to apply this code of conduct well;

፪.ይህን ደንብ የመፈጸም፣ የማስፈፀምና የመከታተል፤

፫. የሥነ-ምግባር መርሆዎችን አፈፃፀም በተቋሙ ተግባራዊ መሆኑን የመከታተል፤

ኃላፊነት አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሥነ-ምግባር መርሆዎች

### ፭. ታማኝነት

ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ፡-

፩. ሕገ መንግስቱን ማክበር፣ ማስከበር፣ ለህዝብ ፍፁም ታማኝ መሆን፤

፪. የመንግስት፣ የህዝብ ሀብት፣ ንብረት እና የሥራ ጊዜን ለመንግስት እና ለህዝብ አገልግሎት ብቻ ማዋል፤

፫. በሥራ አጋጣሚ የተገኘን መረጃ ለህዝብ እና ለመንግስት በሚጠቅም እና የሞራል ተቃርኖ በሌለው አግባብ ጥቅም ላይ ማዋል፤

፬. ራስን ከስርቆት፣ ከማጭበርበር፣ ከማታለል እና ከሌሎች የሙስና ድርጊቶች ነፃ ማድረግ፤

፭.ራስን ማረም፣ በወቅቱ ማስተካከል እና ለተፈጠሩ ስህቶች ይቅርታ የመጠየቅ፤

፮. የመንግስትን ንብረት መጠበቅ እና በጥንቃቄ መያዝ፤ እና

፯. ለቃል ታማኝ መሆን፤

አለበት፡፡

### ፮. ሐቀኝነት

ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ፡-

፩. በመረጃ፣ በእውነት እና በምክንያታዊነት ላይ ተመስርቶ ውሳኔ መስጠት፤ እና

፪. የተዛባ ፍትህ እንዲስተካከል እና እንዲታረም በእውነት ላይ በመቆም ግላዊ ኃላፊነቱን መወጣት፤

አለበት፡፡

2. To carry out, enforce and monitor this regulation;
3. To monitor the implementation of ethical principles in the institution;

## Part two

## Ethical principles

### 5. Loyalty

Any appointee or employee shall:-

1. Respect the constitution, to enforce it, to be absolutely loyal to the people;
2. Spend government, public resources, property and work time only for government and public service;
3. Use the information obtained in the work opportunity in a way that is beneficial to the public and the government and does not have moral contradictions;
4. Free himself from theft, fraud, deception and other corrupt practices;
5. Correct himself in a timely manner and apologize for mistakes made;
6. Safeguard and safekeeping of government property; and
7. Be faithful to his word;

### 6. Honesty

Any appointee or employee shall:-

1. Make decisions based on information, truth and reason; And
2. Fulfilling personal responsibility by standing on the truth so that distorted justice can be corrected and rectified.

## ፯. ቅንነት

ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ፡-

፩.በጎ እና ሥነ-ምግባራዊ ባህሪን በመላበስ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት፤

፪.በሚመራው መሥሪያ ቤት ውስጥ ጠንካራ የሥራ ግንኙነት እና መስተጋብር እንዲኖር ለሠራተኛው እና ለህብረሰተሰቡ ቅርብ መሆን፤

፫.ሥራን ከሚያውኩ ተግባራት መቆጠብ እና ከሚያውኩ አካላት ጋር ባለመተባበር ሥራን በቅንነት ማከናወን፤

፬.በሥራ ሂደት የተፈጠሩ ስህተቶችን በወቅቱ ማስተካከልና፣ አስተያየት መቀበል፤

፭.በሥራ ሂደት ያገኘውን ልምድ እና እውቀት ለህዝብ እና ለመንግስት ጥቅም ብቻ ማዋል፤ እና

፮. መልካም ሥነ-ምግባር በማሳየት ሥራውን በከፍተኛ ሙያዊ ብቃት ጥንቃቄና ትጋት ማከናወን፤

አለበት፡፡

## ፰. ሚስጢር መጠበቅ

ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ፡-

፩. በህግ ሚስጢር ናቸው ተብለው የተለዩ ጉዳዮች ተጠብቀው እንዲያዙ ማድረግ፤

፪. ይፋ ያልተደረጉ ወይም ወቅታቸውን ጠብቀው ይፋ መደረግ ያለባቸውን የመሥሪያ ቤት ሚስጢራዊ መረጃዎችን ህጋዊ በሆነ መንገድ ለህዝብ እና ለሚመለከተው አካል እስኪገለፅ ድረስ በሚስጢር መያዝ፤

## 7. Sincerity

Any appointee or employee shall:-

1. Provide appropriate service by dressing in good and ethical behavior;
2. Be close to the employee and the community in order to have a strong working relationship and interaction in the office he leads;
3. Refrain from activities that disrupt work and to carry out work honestly without cooperating with disruptive entities;
4. Timely correct of mistakes made in the work process and receiving comments;
5. Use the experience and knowledge gained in the course of work only for the benefit of the public and the government; and
6. Perform the work with high professionalism, care and diligence by showing good ethics;

## 8. Keeping a secret

Any appointee or employee shall:-

1. Ensure that matters identified as secret by law are protected.
2. Keep confidential information of the office that has not been disclosed or should be disclosed in a timely manner until it is disclosed to the public and the relevant party in a legal manner;

፫. በሥራ አጋጣሚ ያወቀውን ሚስጢራዊ መረጃ ወይም ጉዳይ ለማይመለከተው እና ማወቅ ለማይገባው አካል አሳልፎ አለመስጠት፤ እና

፬. መሥሪያ ቤቱን ከለቀቀ ወይም ወደ ሌላ ሥራ ከተዛወረ በኋላም ቢሆን በሥራው ምክንያት ያወቃቸውን ሚስጢራዊ መረጃዎች መጠበቅ አለበት፤

፭. በዚህ አንቀፅ የተዘረዘሩት መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጥፋትን ለማጋለጥ ለሚመለከተው አካል ሚስጢራዊ መረጃን ማሳወቅ እንደሚስጢር ማባከን አይቆጠርም፡፡

## ፱. ግልፅነት

ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ፡-

፩. የተቋሙን ተልዕኮ፣ ተግባር፣ ኃላፊነት፣ ደንቦችን፣ የአሰራር መመሪያዎችን የባለጉዳዮች መብትና ግዴታዎችን ለዜጎች ግልፅ ማድረግ፤

፪. የተቋሙን እቅድ፣ አፈፃፀም፣ ውሳኔዎች፣ ትዕዛዞች እና ሌሎች መረጃዎችን ለዜጎች በየወቅቱ ተደራሽ ማድረግ፤

፫. አግባብ ባለው ህግ ሚስጢር ናቸው ተብለው ከተቀመጡት መረጃዎች በስተቀር ለዜጎች ማንኛውንም መረጃ መስጠት፤

፬. ለሚመለከታቸው አካሎች የሚሰጡ መረጃዎች ሁሉ ትክክለኛ፣ ተደራሽ እና ወቅታዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

3. Not to disclose confidential information or matters that he has learned in the course of work to a party that is not concerned and should not know, and
4. Even after leaving the office or transferring to another job, must protect the confidential information he has come to know as a result of his work;
5. Disclosure of confidential information to the relevant party to expose a crime while maintaining the principles listed in this article is not considered to be a waste of secrets.

## 9. Transparency

Any appointee or employee shall:-

1. Clarify the institution's mission, functions, responsibilities, rules, operational guidelines, the rights and obligations of the users to the citizens;
2. Make the plan, implementation, decisions, orders and other information of the institution accessible to citizens periodically;
3. Provide citizens with any information except for the information that is said to be secret according to the relevant law;
4. Ensure that all information provided to relevant bodies is accurate, accessible and up-to-date;

፬. የተቋሙን የአሰራር ሥርዓት፣ አደረጃጀትና የሰው ሀይል አቅም በየጊዜው በመፈተሽ ችግር ያለባቸውን በማሻሻል ህብረተሰቡን የሚያረካ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፤

፭. የተመደበለትን በጀት፣ ጥቅም ላይ የዋለውን መጠን፣ በብድር የተገኘውን እና ለኢንቨስትመንት የዋለውን መዋዕለ ንዋይ በተመለከተ ለህዝብ እና ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል በሪፖርት ማሳወቅ እና ኦዲት ማስደረግ፤

፮.በሚመራው ተቋም ግልፅ እና የሚታወቅ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ተቋማዊ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት፡፡

## ፲፩. ተጠያቂነት

ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ፡-

፩. ለተሰጡ ውሳኔዎች የጋራ እና የተናጠል ኃላፊነት መውሰድ፤

፪. በተመደበበት የኃላፊነት ደረጃ ለሠራው ሥራም ይሁን እንዲሰራ ለአደረገው ሥራ ኃላፊነት መውሰድ፤

፫. በወሰነው ውሳኔ ምክንያት ለሚቀርብበት ጥያቄ እራሱን ዝግጁ ማድረግ እና በተፈለገበት ቦታ እና ጊዜ መገኘት፤

፬. በሚመራው ተቋም ውስጥ ህግ እና ሥርዓትን ተላልፈው የሚገኙ ኃላፊዎችና ሠራተኞችን ተጠያቂ ማድረግ አለበት፡፡

## ፲፪. አድሎ አለመፈፀም

ማንኛውም ተሿሚ እና ሠራተኛ: -

፩. በቀለም፣ በዘር፣ በኃይማኖት፣ በፆታ፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካባቢ፣ በዘመድ፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ልዩነት ሳያደርግ ፍትሀዊ ውሳኔ መስጠት፤

Regularly check the institution's operating system, organization and human resources capacity and improve those that have problems so that it can provide services that satisfy the society;

5. Inform the public and the concerned party about the allocated budget, the amount used, the loan obtained and the investment used for investment in a report and conduct an audit;
6. Fulfill his institutional responsibility by establishing a clear and well-known operating system in the institution he manages.

## 10. Accountability

Any appointee or employee shall:-

1. Take joint and individual responsibility for decisions made;
2. Take responsibility for the work he has done or for the work he has made done at the assigned level of responsibility;
3. Be ready for any question that may be asked as a result of the decision made and to be present at the required place and time;
4. Hold responsible the officials and an employee who violate the law and order in the institution he manages.

## 11. Non-discrimination

Any appointee and employee shall:-

1. Make fair decisions without discrimination based on color, race, religion, gender, political opinion, location, family, disability or any other condition;

፪. በምክንያት፣ በእውነት እና በህግ የተደገፈ ሚዛናዊ ውሳኔ መስጠት፤

፫. ለአድሎዊ አሰራር በር የሚከፍቱ የህግ ማዕቀፎችን እና የአሰራር ክፍተቶችን የሚሞላ ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

፲፫. **<u>አርአያ መሆን</u>**

ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ፡-

፩.የሙያ ክህሎትን፣ የቡድን ሥራን እና የለውጥ አመራር ብቃቱን በማጉልበት ውጤታማ ተቋም መፍጠር፤

፪.የኃላፊነት ስሜት የሚሰማው፣ የተሻለ ለውጥን የሚደግፍ፣ የመሥሪያ ቤቱን መልካም ስም የሚጠብቅና የአሰራር ባህል እንዲዳብር መተማመን ሥር እንዲሰድና ፀንቶ እንዲቆይ መስራት፤

፫.የሀገሪቱን ፖሊሲ፣ ሕጎች፣ ደንቦች በማክበር፣ መፈጸምና ሌሎች እንዲፈጽሙት ማድረግ፤

፬.የሕዝብን ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶችን ማክበር፤

፭.ሱስ እና አደንዛዥ እፆች ነፃ መሆን፤

፮. በሚመራው ወይም በሚሰራበት ተቋም ወቅታዊ እና ሀገራዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ውስጥ ማስገባት፤

፯. በሚኖርበት አካባቢ ወይም የተቋሙን ሥራ በሚመራበት ወይም ሌላ ሥራ በሚያከናውንበት ጊዜ ምሳሌ በመሆን ከፍ ያለ የአርያነት ፀባይ ማሳየት አለበት፡፡

2. Make balanced decisions based on reason, truth and law;

3. Should establish a system to fill legal and procedural framework gaps that open the door to discrimination.

**12. <u>Be a role model</u>**

Any appointee or employee shall:-

1. Create an effective institution by emphasizing professional skills, teamwork and change leadership;

2. Develop a work culture that feels responsible, supports better change, protects the reputation of the office, and works so that trust takes root and remains firm;

3. Comply with the country's policy, laws, regulations, and make sure others comply with it;

4. Respect the cultural and religious values of the people;

5. Be Free from addictions and drugs;

6. Take into account the current and national conditions of the institution he leads or works in, putting him in a continuous process of change;

7. Show a high exemplary character by being an example in the area where he lives or when he manages the work of the institution or performs other work.

**፲፫. ህግን ማክበር**

ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ፡-

፩. የሀገሪቱን ሕገመንግሥት ፣ ሕጎች፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ፖሊሲ እና በዚህ ደንብ የተቀመጡ መርሆችን ማክበር፤

፪. በህግ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ውስጥ ብቻ በመሆን ህግን ባከበረ መልኩ ኃላፊነቱን መወጣት፤

፫. በሥራ ቦታ ህጎችን ማክበር እና ከፀብ አጫሪነት ተግባራት መቆጠብ፤

፬. የሥራ ሰዓት ህጎችን ማክበር፤

፭. ሁሉንም ሰው በእኩልነት ማየትና የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፤

፮. ከጾታዊ ትንኮሳ እና ሌሎች ህገወጥ ከሆኑ ተግባራት በመቆጠብ ለህግ መከበር አስተዋፅኦ ማድረግ፤

፯. በሚመራው ተቋም ውስጥ የመልካም ሥነ-ምግባር እሴቶች ግንባታ መርሆችን እና የሙስና መከላከል ህጎችን መፈፀም እና ማስፈፀም አለበት፡፡

**፲፬. ለሕዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት**

ማንኛውም ተሿሚ እና ሠራተኛ ፡-

፩. ለባለጉዳዮች ተገቢውን አክብሮት በመስጠትና ትህትና በማሳየት ለሚቀርብለት ጥያቄ በአጭር ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት፤

፪. ባለጉዳዩች ግራ ሊጋቡ፣ ትዕግስት ሊያጡና ሊናደዱ ስለሚችሉ በትዕግስት ማስተናገድ አለበት፡፡

**13. Compliance with Law**

Any appointee or employee shall:-

1. Comply with the country's constitution, laws, international agreements, policies and principles set forth in this regulation;
2. Fulfill the responsibility in a manner that respects the law by being only within the duties and responsibilities given by the law;
3. Comply with workplace rules and refraining from violent acts;
4. Comply with laws of working hours;
5. Treat everyone equally and ensuring the rule of law;
6. Contribute to law enforcement by refraining from sexual harassment and other illegal activities;
7. Implement and cause the implementation of the principles of building good moral values and anti-corruption laws in the institution.

**14. Respond appropriately to public inquiries**

Any appointee and employee shall:-

1. Respond to the request in a short time by showing due respect and humility to the stakeholders;
2. Handle with patience as the customers may become confused, impatient and angry.

**፲፭. <u>የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም</u>**

ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ፡-

፩. የግል ጥቅሙን፣ የቤተሰቦቹን ፣ የሌላ ሶስተኛ ወገን ወይም ቡድን ሳይሆን የህብረተሰቡን ጥቅም መሰረት በማድረግ ሥራውን ማከናወን፤

፪. ከመደበኛ ሥራው ጋር ሊጋጭ የሚችልን ማንኛውም ዓይነት ጥቅም ማሳወቅ፤ ግጭቱን ማስወገድ አለበት፡፡

**፲፮. <u>ሕጋዊ በሆነ ስልጣን መገልገል</u>**

ማንኛውም ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ፡-

፩. ህብረተሰቡን በአግባቡ እንዲያገለግል ፣ ኃላፊነቱን እንዲወጣ የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት በህግ ተወስኖ በተሰጠው የስልጣን ገደብ ውስጥ መጠቀም፤

፪. አዋጅን፣ ደንብን ወይም መመሪያን መሠረት በማድረግ ሥራውን ማከናወን አለበት፡፡

**<u>ክፍል ሶስት</u>**

**<u>የሥነ-ምግባር ጥሰቶች እና እርምጃ አወሳሰድ</u>**

**፲፯. <u>የሥነ ምግባር ጥሰቶች</u>**

በዚህ ደንብ የተዘረዘሩ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን አለመፈፀም የሥነ-ምግባር ጥሰት ነው፡፡

**፲፰. <u>ቀላል የሥነ-ምግባር ጥሰቶች</u>**

በዚህ ደንብ አንቀፅ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፫)፣ (፬) እና (፭)፣ አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፪)፣ አንቀፅ ፰ ንዑስ አንቀፅ (፪)፣ (፬)፣ (፭) እና (፮)፣ አንቀፅ ፱ ንዑስ አንቀፅ (፪)፣ (፬) እና (፭)፣ አንቀፅ ፲ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣ (፪)፣ (፫)፣ (፭)፣ (፮) እና (፯) ፣ አንቀፅ ፲፩ ንዑስ አንቀፅ (፬)፣ አንቀፅ ፲፪ ንዑስ አንቀፅ (፪) እና (፫)፣ አንቀፅ ፲፫ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣ (፪)፣(፫)፣ (፮) እና (፯)፣ አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀፅ (፭)፣ (፮) እና (፰) ፣አንቀፅ ፲፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) ፣አንቀፅ ፲፮ ንዑስ አንቀፅ (፪) ቀላል የሥ-ነምግባር ጥሰት ናቸው ፡፡

**15. <u>Prioritizing public interest</u>**

Any appointee or employee shall:-

1. Carry out the work based on the interest of the society, not the personal interest, the family, any third party or group;
2. Disclose any interest that may conflict with the normal work and make sure that the conflict is avoided.

**16. <u>Serving in lawful capacity</u>**

Any appointee or employee shall:-

1. Serve the society properly, to use the authority and responsibility given by the law within the limits of the authority;
2. Perform his work in accordance with Proclamation, regulation or directive.

**<u>Part three</u>**

**<u>Violations of Ethical Principles and Measures</u>**

**17. <u>Violations of Ethics</u>**

Failure to adhere to the ethical principles outlined in this Regulation shall constitutes an ethical violation.

**18. <u>Minor Discipline Violations</u>**

Sub Article (3), (4) and (5) of Article 6, Sub Article (2) of Article 7, Sub Article (2), (4), (5) and (6) Article 8, Sub Article (2), (4) and (5) of Article 9, sub-article (1), (2), (3), (5), (6) and (7) of Article 10, Sub Article (4) of Article 11, Sub Article (2) and (3) Article 12, Sub Article (1), (2), (3), (6) and (7) Article 13, Sub-sections (5), (6) and (8) of Article 14; sub-Article (1) and (2) of Article 15, sub-article (2) of Article 16 of the regulation are Minor Discipline Violations.

**፳. <u>ከባድ የስነምግባር ጥሰቶች</u>**

በዚህ ደንብ አንቀፅ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣ (፪) እና (፮)፣አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣ አንቀፅ ፰ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፫)፣ አንቀፅ ፱ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፫) ፣ አንቀፅ ፲ ንዑስ አንቀፅ (፬) ፣ አንቀፅ ፲፩ ንዑስ አንቀፅ (፩) ፣(፪) እና (፫) ፣ አንቀፅ ፲፪ ንዑስ አንቀፅ (፩) ፣አንቀፅ ፲፫ ንዑስ አንቀፅ (፬) እና (፭)፣ አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣(፪)፣(፫)፣(፬) እና (፯) ፣ አንቀፅ ፲፮ ንዑስ አንቀፅ (፩) ፣አንቀፅ ፲፯ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) ከባድ የስነምግባር ጥሰት ፡፡

**፳፩. <u>የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ</u>**

፩. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት ልማት ድርጅት ተሿሚ የሥነ-ምግባር ጥሰት ሲፈፅም የሥነ ምግባር ክፍሉ ተሿሚው የፈፀመው የጥፋት ዓይነት የተፈፀመበት ጊዜና መረጃ በማደራጀት ለኮሚሽኑ ይልካል፤ ኮሚሽኑ በተላከለት መረጃ መሰረት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ጥፋተኛ ነው ብሎ ሲያምን የዲሲፕሊን ቅጣት እንዲወሰንበት ወይም አግባብነት ያለው የእርምት እርምጃ እንዲወሰን እንደአግባብነቱ የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤት፣ ለከንቲባ ወይም ለተቋም ኃላፊ ያቀርባል፤

፪. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ የሥነ-ምግባር ጥሰት ሲፈፅም የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ የሚመራው በአስተዳደሩ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ወይም በሚተዳደሩበት ደንብ መሰረት ይሆናል፤

**19. <u>Serious Violations of Conduct</u>**

Article 6 sub-article (1), (2) and (6), Article 7 Sub Article (1), Article 8 sub-article (1) and (3), Article 9 sub-article (1) and (3), Article 10 Sub Article (4), Article 11 Sub Article (1), (2) and (3), Article 12 Sub Article (1), Article 13 Sub Article (4) and (5), Article 14 Sub Article (1) ), (2), (3), (4) and (7), Article 16 Sub Article (1), Article 17 Sub Article (1) and (2) of this regulation are serious misconduct.

**20. <u>Taking disciplinary action</u>**

1. When any appointee of a Public Office or government Public Enterprise commits an ethical violation, the ethics department shall organize and send the information to the Commission regarding the time and type of offense committed by the appointee; Based on the information sent, the Commission makes a proper investigation and if the Commission believes that he is guilty it shall make a proposal to the council or the mayor or the head of the institution as appropriate for disciplinary punishment or appropriate corrective action;
2. If any civil servant commits a violation of ethics, the disciplinary action will be governed by the Administration's civil servants Proclamation and the Regulations issued following the Proclamation or the Regulations under which they are governed;

፫. የልማት ድርጅት ሠራተኞች የሥነ-ምግባር ጥሰት ሲፈፅም የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ የህብረት ስምምነት እና የልማት ድርጅቱን የዲሲፕሊን ህጎች መሰረት በማድረግ የሚፈፀም ይሆናል፤

፬. ማንኛውም የህዝባዊ ድርጅቶች ሠራተኛ የሥነ-ምግባር ጥሰት ሲፈፅም የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

**፳፪. ተደራራቢ ክስ የተከለከለ ስለመሆኑ**

፩. የሥነ-ምግባር ጥሰት የፈፀመ ማንኛውም ተሿሚና ሠራተኛ በዚህ የሥነ-ምግባር ደንብና በአስተዳደሩ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ በተደነገገው መሰረት በአንድ ጊዜ በተደራራቢነት ሊቀጣ አይገባውም፤

፪. በአስተዳደሩ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ እና በዚህ ደንብ በሁለቱም የሚያስቀጣ ጥፋት የተፈፀመ እንደሆነ ጉዳዩ በመጀመሪያ በቀረበበት ህግ መሰረት ብቻ ይታያል፤

፫. በሥነ-ምግባር ጥሰት የተቀጣ ተሿሚና ሠራተኛ የይግባኝ መብት የተጠበቀ ነው፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፫. ጥቆማ ስለማሳወቅ**

፩. ማንኛውም ተሿሚና ሠራተኛ በዚህ ደንብ ውስጥ የተካተቱ መርሆዎችን የሚፃረር የሥነ-ምግባር ጥሰት መፈፀሙን በማንኛውም መንገድ ካወቀ ወይም ከተመለከተ ጉዳዩን ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ጥፋቱ ከበድ ያለ ከሆነም ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት፤

3. When employees of a Public Enterprise commit an ethical violation, disciplinary action will be taken based on the collective agreement and the disciplinary rules of the Public enterprise;

4. When any employee of public organizations commits an ethical violation, disciplinary action will be taken according to the relevant law.

**21. Prohibition of concurrent charges**

1. Any appointee or employee who commits a violation of ethics shall not be subject to concurrent charges of the provisions of this code of conduct and the administration's government employees' Proclamation and the regulations issued to enforce the proclamation;

2. If an offense punishable by both the Civil Service Proclamation of the administration and this regulation has been committed, the case will be seen only according to the law in which it was presented first;

3. The right of appeal is reserved for an appointee or employee who has been punished for an ethical violation.

## Part four
## Miscellaneous provisions

**22. Duty to report**

1. Any appointee or employee who learns or observes in any way that an ethical violation has been committed against the principles Provided in this regulation, must report the matter to the Ethics Liaison office, or if the offense is serious, to the Commission;

፪. የሚያቀርበው ጥቆማ እውነተኛ፣ ያልተዛባ፣ ከበቀል የፀዳ፣ አሳሳች ያልሆነና ምክንያታዊ በሆነ እምነት ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል፤

፫. ጥቆማ አቅራቢው ከማንኛውም የበቀል ጥቃት የመጠበቅ መብት አለው፤

፬. ጥቆማ አቅራቢው ማንነቱ እንዳይገለጽ ከፈለገ ማንነቱ በሚስጥር መያዝ አለበት፡፡

**፳፫. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፬. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፭. <u>መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን</u>**

ኮሚሽኑ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፮. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከ መጋቢት ፯ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፯ ቀን <u>፪ሺ፲፭</u> ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ ደሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

2. The Reports he makes must be true, unbiased, free of revenge, non-misleading and based on a reasonable belief;
3. The whistleblower has the right to be protected from any retaliation;
4. If the whistleblower wishes to remain anonymous, his identity must be kept confidential.

**23. <u>Duty to cooperate</u>**

Any person shall be duty-bound for the implementation of this Regulation.

**24. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any Regulation or Directive or customary practices of the cabinet which are inconsistent with this Regulation shall have no effect.

**25. <u>Power to Issue Directives</u>**

The Commission may issue directives that are necessary for the implementation of this Regulation.

**26. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force as of this 16th day of March 2023.

**Done at Addis Ababa, this 16th day of March 2023.**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**